# የግንቦት 7 የኤርትራ ጉባኤ
# "ህጻናት ጠባቂው"

በአራተኛው ክፍል ያቀረብነው የአርበኞች ግንቦት 7 የኤርትራ ጉባኤ ሪፖርታዥ ላይ በቀሩት ሶስት አጀንዳዎች ዙርያ የተካሄደው "ውይይት" በተለይ ደግሞ ግንቦት 7 አማራውን ከትግል ሜዳ ለማስወገድ በቀየሰው ስልት መሰረት የአርበኞች ግንባርን ህልውና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት በሻዕቢያና በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የተካሄደውን ሴራ ማስነበባችን ይታወሳል፡፡

በዚህ ጉባኤ ላይ የተሳተፉት ምንጮቻችን ስለ ግንቦት 7 መሪዎች በተለይ ደግሞ ስለ ሊቀመንበሩ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የታዘቡትን አስገራሚና አስመሳይ ባህርያት በተመለከተ በብዕራቸው የተረኩልንን በተከታታይ የምናቀርብ ይሆናል፡፡ ......

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ለረጅም ጊዜ አውቀዋለሁ፡፡ በአካል ሳገኘው ግን ሁሌም የሚገርመኝ የማይጨበጥ ባህሪይ አለው፡፡ እንደቦታውና እንደሁኔታው እንደ እስስት የሚቀያየር ችሎታው በጣም ይደንቀኛል። ከሰራዊቱ ጋር ሲሆን ዲያስፖራውን ሲያማና ሲያዋርድ ታገኘዋለህ፡፡ ከዲያስፖራው ጋር ሲገናኝ ደግሞ ባለፈው ፅሑፌ እንደገለፅኩት ሰራዊቱ ፈሪ፣ ግዳጅ ሲሰጠው የሚሸሽ፣ መሳርያውን የሚሸጥ ከስልጠናና ከትምህርት የሚቀር... ወዘተ እያለ ተስፋ እንደሌለው አድርጎ ሲሳለቅ ትሰማለህ፡፡ በአንፃሩ እርሱ የሚወዳቸውን ቤተሰቦቹን አሜሪካ ትቶ ኤርትራ በረሃ ውስጥ ለትግል የከተመ አስመስሎ በራሱና በተላላኪዎቹ ወሬውን ሲያናፍስ ስትሰማው ጉድ ያሰኝሃል፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከተለያዩ የአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ሃገራት የተሰበሰበው የድርጅቱ አባል አስመራ ከገባ በኋላ ይመቹኛል ያላቸውን በተናጠል ሲያነጋግር ከቆየ በኋላ የርሱን ሃሳብ ይቀበላሉ ያላቸውን ደግሞ በመለየትና በተወሰነ ቁጥር በማሰባሰብ ሲያነጋግረን ነበር፡፡ በተሳተፍንባቸው በእነዚህ የተናጠል የቡድን ውይይቶች ለጉባኤተኛው ካቀረበው ሪፖርት ውጪ ከዚህ በፊት የገጠሙት ችግሮች በቁጥጥር ስር ማዋል እንደቻለ፣ በቀጣይም ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ፣ የአርበኞች ግንቦት 7 አመራርን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግና የሽፍቶች ስብስብ የሚለውን አርበኞች ግንባርን ከትግል ሜዳው ለማስወገድ ባካሄደው እልህ አስጨራሽ ትግልና ባለፈባቸው ውጣ ውረዶች ሁሉ የኤርትራ መንግስት ባለስልጣናት ሙሉ እገዛ እንደነበረው፣ በተለይ የቅርብ አለቃው የሆነው ኮ/ል ፍፁም በኢትዮጵያ የተቃውሞ የትግል ታሪክ ውስጥ እስካሁን ያላየው በእሱ (ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ) የአመራር ብቃትና ችሎታ እየተደነቀና ከፍተኛ እምነትም እያሳደረ መምጣቱን በመግለፅ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ባህልና ስነምግባር ውጪ ያለ ሃፍረት አፉን ሞልቶ ደረቱን ነፍቶ ሲናገር ለሚሰማው በጣም ያሳፍራል፣ ያሸማቅቃል።

የድርጅቱ አባል የሆነው ዲያስፖራ ተመርጦ ለጉባኤ ወደ ኤርትራ ከመግባቱ በፊት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አስመራ ከተማ ያለ ስራ ከተቀመጡ የድርጅቱ አባል የሆኑ ወጣቶች ጋር የኢሳት ቢሮ በሚባለው ቪላ ውስጥ ተደጋጋሚ ስብሰባ ሲያካሄድ ነበር፡፡ በዚህ ስብሰባም እነዚህን ወጣቶች እንደየሁኔታ

በተናጠልና በቡድን እንዲሁም አንዳንዴ ነአምን ዘለቀን ሌላ ጊዜ ደግሞ ከኤፍሬም ማዴቦ ጋር ሲያሻው ደግሞ ሁለቱን ይዞ (ነአምንና ኤፍሬም) ሲያነጋግራቸው ነበር፡፡
በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ፡-

- የኤርትራ መንግስት በኛ (በግንቦት 7 ማለቱ ነው) መልፈስፈስ ምክንያት በሙሉ ልብ ሊደግፈን መቸገሩን፤
- በተለይ እዚህ ኤርትራ ውስጥ ያላችሁ ወጣቶች የሚከፈለውን ሁሉ ዋጋ ከፍላችሁ ራሳችንን እንድናጠናክር ኃላፊነት መውሰድ አለባችሁ፤
- ያለንን አቅምና ዘዴ በሙሉ ተጠቅመን የጉባዔ እንቅፋቶችን መጥረግና ጉባዔው እንዲሳካ ማድረግ አለባችሁ፤

በማለት ሲያነጋግራቸው እንደነበር የሚስታውሱት እነዚህ ወጣቶች ዲያስፖራዎች ሲመጡ ደግሞ በአንዴ ተገልብጦ የኤርትራ ባለስልጣኖችን ሚና እያገዘፈ በቅርብ የተናገረውን ረስቶ ለራሳቸው ጭምር እንግዳ የሆነ አቋም ሲያንፀባርቅ በመስማታቸው መደናገራቸውን ሳይሸሽጉ በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አስገራሚ ባህርይ በአጠቃላይ ግራ መጋባታቸውን በጉባኤው ላይ በግልፅ ያነሱበት ሁኔታ ነበር።

ከዚህ አልፎ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዶ/ር ብርሃኑ በዲያስፖራው ላይ ያለውን ጥላቻና ንቀት ለእነዚህ ወጣቶቹ ሲገልፅ

- ዲያስፖራው ተስፈኛ ነው፤
- በእናንተ ደምና መስዋዕትነት ስልጣን እንዲይዝ ዕድል መስጠት የለብንም፣
- የትግሉ መሪ መሆን ያለባችሁ እዚህ ያላችሁ ወጣቶችና ወደ ኤርትራ ለመግባት ፈቃደኛ የሆኑት ብቻ ናቸው፤
- በአሁኑ ሰዓትም ለታይታ እንጂ የእናንተን ያህል ትግሉ ገብቶት ለትግሉ አስተዋፅኦ የሚያደርግ የውጭ አመራር የሚባል የለም፤
- ውጭ ያለው "የድርጅቱ አባል ተብዬም" አብዛኛው ለፖለቲካ ጥገኝነት የድጋፍ ደብዳቤ ለመጠየቅ የተሰበሰበ ነው፣ ወረቀት ለመግዛት ተክሌ ይሻው ዘንድ ሄዶ መሰለፍ ይችላል፤
- በውጭ ሃገር የሚገኙ አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች በመሪ አምልኮ የተለከፉ ከመሪ ጋር ፎቶ እየተነሱ ኢንተርኔት ላይ በመለጠፍ በትግሉ ላይ የሚቀልዱ ናቸው፤
- በፋይናንስም ሆነ በማቴሪያል ከዲያስፖራው የሚጠቅመን ድጋፍ እያገኘን እንዳይመስላችሁ"

በማለት ሲያማና እሮሮ ሲያሰማ በቆየ አንድ ሳምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተገልብጦ ዲያስፖራው በተገኘበት ጉባኤ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዲያስፖራው አባላችን 33 ሚሊዬን ብር አግኝተናል ተብሎ በዲያስፖራው የብርሃኑ ገንዘብ ያዥ እንደሆነ በሚታወቀው በተስፋዬ ለታ (ሁሉቃ) አማካይነት ለተሰብሳቢው ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረጉ ያሳፈራቸው መሆኑን እነዚህ ወጣቶች በአደባባይ ሲናገሩ ሰምተናል፡፡

ይህ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ የግንቦት 7 ትግል አለ ብለው ወደ ኤርትራ የገቡና በረሃብና በእርዛት ተሰቃይተው የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ሲሉ በሻዕቢያ የእርሻ ማሳዎች ላይ በከባድ የጉልበት ስራ ኮስምነው ከሰውነት ውጪ ሆነው ያገኛቸውን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ቢያንስ ከኛ የተሰበሰበው ይህ ሁሉ ገንዘብ ታድያ የት ገባ? ብሎ ለመጠየቅ የደፈረ አንድም ዲያስፖራ አለመገኘቱ በጣም ያሳዝናል፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ እስስት ባህርዩ በውጭ ሃገር በሚገኘው የድርጅቱ አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የመረረ ጥላቻ እንዳለው ለማስመሰል ይሞክራል፡፡ እነዚህ ወጣቶች “በሚቀጥለው የአመራር ምርጫ ላይ ለህይወታቸውና ለምቾታቸው የማይሳሱ፣ እዚህ ኤርትራ "በረሃ" ጠቅልለው መግባታቸውን ያረጋገጡልን ብቻ ነው ለአመራርነት የምንቀበለው” ሲላቸው መክረሙን ይናገራሉ፡፡ አዲስ በተባለው የመዋቅር ማሻሻያም እነዚህን ወጣቶች ለማታለል የውጭ ጠቅላላ ጉባዔና የውጭ ምክር ቤት የሚባለው ቀርቶ ውጭ የሚኖረው የድርጅቱ አመራር ተቀማጭነቱን አስመራ ባደረገ ዘርፍ ስር እንዲገባ ለማድረግ ተሞክሯል።

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ዶ/ር ብርሃኑ ጊዜና ወቅት እየተከተለ በሰዎች ላይ ያለው እይታ የሚቀያየር መሆኑ ነው፡፡ አንዳርጋቸው ፅጌ በወያኔ ከመያዙ በፊት “ከውቤ (ብዙነህ ፅጌ) በስተቀር የሚረባ የውጪ አመራር የሚባል ሰው የለንም” ሲል እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እንደ ጣኦት ሲያመልከው የነበረው አንዳርጋቸው ፅጌ በወያኔ ተይዞ እስር ቤት ከተወረወረ በኋላ ግን ውቤ ወንድሙን (አንዳርጋቸውን) ያግዛል በሚል ቂም ቋጥሮበት እንደነበር የሚነገረው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በውቤ ላይ የሚሰነዝረው ስድብና ዘለፋ ለመስማት ሁሉ የሚቀፍ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለውቤ ሲያዦረግድ የምናውቀው ዶ/ር ብርሃኑ አሁን ትዕዛዝ የሚያስተላልፍለት በነአምን ዘለቀ በኩል ነው፡፡ ጊዜው የሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስለሆነ በውቤ ላይ የቋጠረውን ቂም መወጣጫና ለሌሎችም ማስተማሪያ ሊያደርገው መፈለጉ ለማስመሰል ያህል እንኳን መደበቅ አልፈለገም። ከድርጅቱ አመራርነት ለማግለል ሲል "ውቤ የህፃናት ጠባቂ ሆኗል" በማለት አሉባልታ ሲያናፍስበት የከረመው ዶ/ር ብርሃኑ ከተንኮል ሴራው አምልጦ ውቤ በዚህ ጉባኤ ለምክር ቤት አባልነት የተመረጠ ቢሆንም እንደ ሙሉነህ እዩኤል በካልቾ እንዲመታ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ወሬ አቀባባይ በሆነው በግርማቸው በኩል ያልተሳካ ሙከራ ሲደረግ ታዝበናል። ይህንን ትዕይንት የተከታተለው ጉባኤተኛ ውቤ በቀጣይ በራሱ ጊዜ ከድርጅቱ ሊለቅ እንደሚችል አልተጠራጠረም፡፡

ውቤ ምክር ቤት ከገባ በኋላ ለስራ አስፈፃሚነት ተጠቁሞ የነበረ ቢሆንም በስራ አስፈፃሚነት ለመመረጥ ምድር ላይ (ኤርትራ) ጠቅሎ መግባት ያስፈልጋል የሚል ቅድመ ሁኔታ በዶ/ር ብርሃኑ ስለተቀመጠ (ለታደሰ ብሩ የማይሰራ) ውቤ "እኔ ነብስ ያላወቁ ህፃናት ልጆች አሉኝ አልችልም" በማለት ለድርጅቱ ስራ አስፈፃሚነት መመረጥ እንደማይፈልግ በማሳወቅ ራሱን ከምርጫ አግልሏል።

ውቤ “ህጻናት ጠባቂ” ሆኗል ለሚለው የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሐሜትና ሽሙጥ የተሰጠ ምላሽ መሆኑ ግልፅ ነበር፡፡

**ይቀጥላል....**